የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፕሬዝደንት ጽሕፈት ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE PRESIDENT

ቀን 30 ሚያዚያ 2010
Date
ቁጥር ፕጽ/ጽ1/2617/2010
Ref. No.

ለመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

ክቡር ፕሬዝደንት የሚያደርጓቸው የተለያዩ የስራ እንቅስቃሴዎች ለመዘገብ የተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ወደ ብሔራዊ ቤተመንግስት እንደሚመጡ ይታወቃል፡፡ ከመገናኛ ብዙሃን ጋር ባለን መልካም የስራ ግንኙነት ደስተኛ ብንሆንም ለዘገባ የሚመጡ አንዳንድ ጋዜጠኞች እና የካሜራ ባለሙያዎች ያላቸው የአለባበስ ሁኔታ የፕሬዝደንሲውን ክብር እና ደረጃ የማይመጥን ከመሆኑም ባለፈ ለሀገር ገፅታ ጭምር አሉታዊ ተፅዕኖ ያለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሆኑም ይህ ደብዳቤ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ ለዘገባ ወደ ብሄራዊ ቤተመንግስት የሚመጡ ጋዜጠኞችና ካሜራ ባለሙያዎች ደረጃውን የጠበቀ አለባበስ እንዲከተሉ ይህ ካልሆነ ግን ለማስተናገድ የምንቸገር መሆኑን በእናንተ በኩል እንዲገለፅላቸው በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ፍቃዱ በቀለ ገመዳ
ኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፕሬዝዳንት
ጽ/ቤት ኃላፊ